# <u>የአንድነት ፓርቲ የሰላማዊ ትግል ቃልኪዳን</u>

- እኔ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን <u>ሕዝብ ጥቅም</u> ለማስቀደም ቃል እገባለሁ::
- እኔ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ከቆመችበት ጊዜ ጀምሮ <u>ሰማዕታት የተሰዉለትን ክቡር ዓላማ</u> ከግብ ለማድረስ ቃል እገባለሁ::
- እኔ በሀገሬ እንደዜጋ <u>ተፈጥሯዊ የሆነውን ነፃነቴን</u> ማንም እንዳይነጥቀኝ በትግሌ ለማስጠበቅ ቃል እገባለሁ::
- እኔ <u>ለልጆቼ በሁለንተናዋ የተመቸች</u> ኢትዮጵያን ለማውረስ ቃል እገባለሁ::
- እኔ <u>ለዴሞክራሲ መርሖዎች</u> ለመገዛት ቃል እገባለሁ::
- እኔ የፓርቲዬን <u>ሕግና ደንብ</u> ለማክበርና ለማስከበር ቃል እገባለሁ::
- እኔ ፓርቲዬ የሰጠኝን <u>ሃላፊነት በታማኝነትና በቅንነት</u> ለመወጣት ቃል እገባለሁ::
- እኔ አንድነት ፓርቲዬ በኢትዮጵያ <u>ጠንካራ አማራጭ የፖለቲካ ኃይል</u> እንዲሆን ለማድረግ <u>በሕይወት፣ በንብረት፣ በጉልበት፣ በዕውቀት</u> እንዲሁም በተቻለኝ ሁሉ ለማገልገል ቃል እገባለሁ::
- እኔ ፓርቲዬ በቆመለት <u>የሰላማዊ ትግል</u> መርሕ <u>ሕዝብን የስልጣን ባለቤት</u> እንዲያደርግ ጠንክሬ ለመስራት ቃል እገባለሁ::
- እኔ ለእውነት ፣ ለፍቅር፣ ለመተሳሰብ፣ ለአብሮነት እንጂ <u>ለግል ጥቅምና</u> ጊዜያዊ ክብር ላልገዛ ቃል እገባለሁ::